# የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ)

Ethiopian People's Revolutionary Party (EPRP)


ሚያዚያ 2 ቀን 2003 ዓ.ም

## የወያኔን አዲስ የዘረፋ እንቅስቃሴ እንቃወም!!

የመለስ ዜናዊ አገዛዝ የማይቀርለትን የሕዝብ አመፅ ለማፈን በውስጥም በውጭ ሀገርም መቅበዝበዝ አብዝቷል። ልሰራው ነው ብሎ በሚለፍፈው ሚሌኒየም ግድብ ተብዬ አማካይነትም ሕዝብን በአዲስ መልክ ሊዘርፍና ይበልጥ ሊያደኸይ ተነስቷልና ሕዝብ ይህን ዘረፋ መቃወምና በእምቢታም መታገል ይኖርበታል።

ይህ 80 ቢሊዮን ብር ያወጣል የሚባለው ግድብ ቀደም ሲል ከጣና በለስና ግልገል ጊቤ ግድቦች በሚገኝ ገቢ ወጪው ይሸፈናል ሲባል የነበረ ሲሆን የመለስ ዘራፊ ቡድን ዞር ብሎ ግን ሕዝብ ወጪውን መጋራት አለበት በሚል በአሁኑ ጊዜ የሚከተለውን በውዴታ መዋጮ ሽፋን ወስኖ በስራ ለማዋል ተነስቷል።

- እያንዳንዱ ሠራተኛ የወር ደሞዙን በዓመት ለግድብ በሚል ይከፍላል፤
- በንግድ ተቋሞች እጅ ያለ ገንዘብ፤ ተጠራቅሞ ያለ የግለሰቦችና የግብረሰናይ ድርጅቶች ገንዘብ (ወደ ዕቁብና ዕድር ገንዘብ ይወርዳልም ተብሏል) ቦንድ መግዣ ይውላል፤
- የገንዘብ ስብሰባው ተስፋፍቶ ሁሉም እንደ ዘመነ ደርግ የውዴታ መዋጮ ተብሎ ይቀርባል።

ግድቡ የዝርፊያ መሣሪያ ሆኖ ሕዝብን በወያኔ ለማስበዝበዝ ምክንያት መሆኑ ከወዲሁ ወያኔን የሚያውቅ ሁሉ የሚገነዘበው ነው። መለስ፤ ሚስቱና ጭፍሮቹ ዘርፈው ባዕድ ሀገር ባንኮች ካስቀመጡት ብዙ ቢሊዮን ብር ውስጥ ለመዋጮ የሚመለስ አለመኖሩም ሳይታለም የተፈታ ነው። መለስ ዜናዊ ፀረ ኢትዮጵያ መሆኑ እየታወቀ ለሀገሪቷ የተቆረቆረ በመምሰል በግብፅና አልፎም በኤርትራ ላይ እያሰማ ያለው ውርጅብኝም ሃላፊነት የጎደለውና ሀገሪቷንም ለጥቃት ሊያጋልጥ የሚችል መሆኑ የሚታይ ነው። በሀገራችን ያለው የዴሞክራሲና ፍትሃዊ አስተዳደር ዕጦትና ሰፍኖ ያለው ዘረኛ የግፍ አገዛዝ ሕዝብን አስቆጥቶ ለዓመጽ እየገፋው በመሆኑ ይህንን ሁኔታ ለማስቆምና ለመሸፋፈን፣ የሕዝብን ዕይታ ወደ ውጭ ለመውሰድ የመለስ አገዛዝና ጭፍሮቹ የሚያካሂዱት አደናጋሪ ቅስቀሳ ማንንም ዜጋ ወያኔን ከመጣልና ከማስወገድ--ከማመፅ--ግዳጁ ሊያዘናጋው አይገባም። ተማሪ፣ አስተማሪው፤ ነጋዴው፤ አውቶቡስና ታክሲ ነጂው፤ ስራ አጡ፤ ሠራተኛውና አርሶ አደሩ ሁሉ ይህን የግፍ አገዛዝ ለማስወገድ በጋራ ማመፅ ግዴታው ነው። ይህን ግዳጅ ከግብ ካላደረሰ ግን ዘራፊና አረመኔው አገዛዝ ይሉኝታ ቢስ ነውና ነጋ ጠባ የብዝበዛና የጭቆና ዘመቻውን ከማጠናከር ወደኋላ የሚል አይደለም። በዓለም አቀፍ ደረጃ ያሉ ኢትዮጵያዊያንም የወያኔን ብዝበዛና ዘረፋ እያጋለጡ፤ ዋናው ችግር ግድብ ያስፈልጋል አያስፈልግም አለመሆኑን እያስረዱ ይህን አረመኔ አገዛዝ ማጋለጥ አለባቸው።

ኢሕአፓም ከሕዝብ ጎን ሆኖ ትግሉን ለማፋፋም እየጣረ ነውና በወያኔ አገዛዝ ላይ ሕዝባዊ አመፅ ማደራጀት ግዳጃችንና ተልዕኮአችን ነው ከሚሉ ኃይሎች ጋር ሁሉ በትግል ሜዳ በሀገር በት ሊተባበር ዝግጁ መሆኑን ዳግም ይገልፃል።


EPRP
P.O.Box 73337
Washington D.C. 20056
U.S.A
Tel. : (202) 291-4217
Fax : (202) 291-7645

EPRP
BP 22
Bois Colombes 92270
France

E-mail ESPIC@aol.com Website: http://www.EPRP.com